የሰበር መ/ቁ.22463

የካቲት 16 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ /አ/ማ/ ጠበቃው ቀርቧል

መልስ ሰጭ፡- 1- አቶ ዮሐንስ ኤዞ, 2- አቶ ሰይፉ ብርሃኑ, 3- አቶ መስፍን አሰፋ, 4- አቶ ዮሐንስ ጋንኤ, 5- አቶ ግርማ ወንድሙ, 6- አቶ ፍሬው ከበደ — አንደኛው መልስ ሰጭ ወክሎ ቀርቧል

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድን ስልጣን የሚመለከት ነው።

በመ/ሰጭዎች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክሱ የቀረበው የተመደብንበት የስራ መደብ ደረጃ ይስተካከል በሚል ነው። አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ለማየት ስልጣን አለው በማለት የተሰጠ ነው። አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል።

ችሎቱም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ውሳኔ ቦርድ የስራ ክርክሮች ምን አይነት ናቸው የሚለውን የህግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበለትን ውሳኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ መርምሯል።

12-7-98

ይህ ችሎት በመ/ቁ.18180 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተርጎም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የውል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ነው፤ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፤ በአንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ /ሰራተኞች/ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት የህግ ትርጉም ሰጥቷል።

መ/ሰጭ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የተመደብንበት የስራ መደብ ደረጃ ይስተካከል በሚል ያቀረበው ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የስራ ክርክር አይደለም። በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን አለው በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

## ው ሳ ኔ

- የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሃምሌ 8 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 41229 ታህሳስ 19 ቀን 1998 ዓ.ም ውሳኔ ተሽሯል።
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ.ፊ 12-7-98